## መመሪያ ቁጥር 1075/2017

## የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የቴክኖሎጂ ሽግግር መመሪያ

በሀገራችን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ውጤታማና ዘላቂ የሆነ የማህበረሰቡን እና የኢንዱስትሪውን ችግር መፍታት ባለመቻሉ፤

ተቋማት ትስስርን መሰረት ባደረገ፣ የማህበረሰቡንና የኢንዱስትሪውን ችግር በሚፈታ መልኩ እንዲሁም ወጥ የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ፤

አነስተኛ የምርምርና ልማት በጀት ችግር ለመቅረፍ ከቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኝ ገቢ እንደ አማራጭ መጠቀም በማስፈለጉ፤

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሻሽሉ፣ የማህበረሰቡን እና የኢንዱስትሪውን ችግር የሚፈቱ ቴክኖሎጂዎችን ለንግድ ሥራ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በትስስር ማዕቀፍ ውስጥ አዲስ የንግድ ፈጠራ ሀሳብ፣ አነስተኛ ግልጋሎት ሞዴል እና ፈጠራ ባለቤትንት መብት ያለቸውን ግልሰቦች ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ውጤታማ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስርጸትን በየዘርፉ ተግባራዊ ለማድረግ ጠንካራ ሀገር አቀፍ የተቋማት ትብብር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር መረጃዎች፣ መሰረተ-ልማቶችን መገንባትና ማጠናከር የሚያስችል ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር ከትስስር ምክር ቤት ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር1298/2015 አንቀጽ 22 ንዑስ-አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## DIRECTIVE No. 1075/2025

## Higher Education, Technical and Vocational Training, Research Institutions, and Industry Linkage Technology Transfer Directive

**WHEREAS,** the technologies transferred are not being able to solve the problems of the community and the industry in an effective and sustainable way;

**WHEREAS,** the lack of a harmonized technology transfer and development system in which institutions are managed based on linkage platform, a way that addresses the problems of community and industry;

**WHEREAS,** the need to use technology transfer as an alternative source of revenue to address the limited research and development budget;

**WHEREAS,** it is necessary to commercialize technology that improve the economy of the country, solve the problems of the society and the industry;

**WHEREAS,** it is important to encourage new business ideas, small business models, and individuals with innovation rights within the framework of connectivity;

**WHEREAS**, it is necessary to establish a system for strong national institutional cooperation, technology transfer information, building and strengthening infrastructure, in order to implement effective technology transfer and dissemination in all sectors;

**THEREFORE,** the Ministry of Education in collaboration with Linkage Council has issued this directive by the provisions on Higher Education, Technical and Vocational Training, Research Institutions and Industry Linkage Proclamation 1298/2023, article 22, sub article 2.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1፡- አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የቴክኖሎጂ ሽግግር መመሪያ ቁጥር** 1075/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2፡- ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"ሚኒስቴር እና ሚኒስትር"** ማለት ትምህርት ሚኒስቴር እና ሚንስትርን የሚያመለክት ነው፤

2/ **"ቴክኖሎጂ"** ማለት ሀገራዊ የኢኮኖሚ፣ የኢንዱስትሪ እና የማህበራዊ ችግሮችን በመቅረፍ የአኗኗር ዘይቤን ለማሻሻል ጥቅም ላይ የዋለ እሴት የተጨመረበት የምርምር፣ የሳይንስና የፈጠራ ውጤት የሆነ ቁስ ወይም ቁስ ያልሆነ እውቀት፣ ጥበብ፣ ሙያ፣ ግኝት፣ የአሰራርና የአመራረት ዘዴ፣ አዲስ ምርት ወይም አገልግሎት ነው፤

3/ **"የንግድ ሥራ ኢንኩቤተር"** ማለት ለጀማሪ ንግድ ተቋማት አጠቃላይ የንግድ እገዛ ፕሮግራም የሚሰጥ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት አሳላጭ ማዕከል ነው፤

## Part One

## General Provision

### Article 1፡ Short Title

This directive may be cited as **"Higher Education, Technical and vocational Training, Research Institutions and Industry Linkage (HETRIIL) Technology Transfer Directive No. 1075/2025."**

### Article 2፡ Definitions

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1/"**Ministry and Minister**" means the Ministry of Education and Minster, respectively;

2/ "**Technology**" means a material or immaterial knowledge, art, profession, discovery, method of operation and production, a new product or service that is the result of value-added research, science and innovation used to improve the quality of life by addressing national economic, industrial and social problems;

**3/** "**Business Incubator**" shall refer to an economic and social developer institute that designed to host, and support potential start-up companies through a comprehensive business assistance program;

4/ **“የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ፓርክ”** ማለት የከፍተኛ ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ክላስተር ሲሆን ቴክኖፖሊስ (በቴክኖሎጂ ያደገ ከተማ)፣ ሳይንስ ፓርክ፣ ቴክኖሎጂ (ኢንዱስትሪያል) ፓርክ፣ የፈጠራ ማዕከል፣ የምርምርና ልማት ፓርክ፣ የዩኒቨርሲቲ ምርምር ፓርክ፣ የምርምር እና የቴክኖሎጂ ፓርክ፣ ቴክኖሎጂ ኢንኩቤተር እና የቴክኖሎጂ ንግድ ኢንኩቤተር የያዘ ስፍራ ነው፤

4/ "**Science and Technology Park**" shall refer to a place that encompasses any kind of high-tech cluster such as: technopolis, science park, high tech (industrial) park, innovation center, R&D park, university research park, research and technology park, technology incubator, and technology business incubator;

5/ **“ጀማሪ የንግድ ስራ”** ማለት በንግድ ሥራ ፈጠራ መሥራቾች አማካኝነት አዲስ የተቋቋመ ወይም በዕድገት ላይ የሚገኝ እንዲሁም የገበያ ፍላጎት ያለውን አዲስ አገልግሎት ወይም ምርት የሚሰጥ ወይም የሚያመርት ድርጅት ነው፤

5/ "**Start-up business**" means a business that is newly established or young company through entrepreneurial founders and provides new services or products that have market demand;

6/ **“ተስማሚ ቴክኖሎጂ”** ማለት ባለበት መልከዓ-ምድራዊ ቦታ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ተስማሚ የሆነ፣ ከአካባቢው ጋር የሚጣጣም እንዲሁም ለሚጠቀሙበት ሰዎች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥርና የሚያበረታታ የተቀመረ ወይም እሴት የተጨመረበት ቴክኖሎጂ ነው፤

6/ "**Appropriate Technology**" shall refer to technology that is suitable to the social and economic conditions of the geographic area in which it is to be applied, is environmentally sound, and promotes self-sufficiency on the part of those using it;

7/ **“የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ሂደት”** ማለት ተስማሚ ቴክኖሎጂን ከመለየት ጀምሮ መምረጥ፣ ማሸጋገር፣ ወደ ገበያ ማስገባት፣ መጠቀም እንዲሁም በአግባቡ የማስወገድ ስራዎችን የሚያካትት ነው፤

7/ "**Technology transfer and development process**" shall refer a process that involves identifying appropriate technology, selecting, transferring, commercializing, utilizing, and properly disposal of the technology;

8/ በትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 አንቀጽ 2 ላይ ትርጓሜ ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፤

8/ Words defined in article 2 of Linkage Proclamation No. 1298/2023 are also used for this directive;

9/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

9/ Any term or provision that references the male gender shall also be inclusive of the female gender.

**አንቀጽ 3፡- የተፈፃሚነት ወሰን**

**Article 3፡ Scope of of the directive**

ይህ መመሪያ በትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 በተጠቀሱት በሁሉም የትስስር አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

This directive applies to the linkage actors mentioned in the Linkage Proclamation No. 1298/2023.

**አንቀጽ 4፡- አላማ**

**Article 4፡ Aim**

የመመሪያው አላማ በትስስር አካላት የሚከናወን የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ትግበራን የተሳለጠ ለማድረግ፣ ቴክኖሎጂዎችን በማበልፀግ እና በማስፋፋት ጀማሪ የንግድ ስራዎችን ለመፍጠር የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርአት መዘርጋት ነው።

The objective of the directive is to establish a technology transfer system to streamline the implementation of technology transfer and development carried out by linkage actors, incubate and expand technologies to create start-up businesses.

## ክፍል ሁለት
## የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር

## Part Two
## Intellectual Property Protection and Technology Transfer

**አንቀጽ 5፡- የአዕምሮአዊ ንብረት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ማዕከል ስለማቋቋም**

**Article 5፡ Establishing an Intellectual Property and Technology Transfer Support Center**

1/ የትስስር አካላት በትስስር የሚከናወኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን ለማሳለጥ የሚያስችሉ በአዋጅ ቁጥር 1298/2015 አንቀጽ 8 ንዑስ-አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 16 መሰረት የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ማእከል ይቋቋማል፤

2/ የትስስር አካላት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንዑስ-አንቀጽ 1 መሰረት በየተቋሙ በተቋቋመው ማዕከል የሚሰጡ አገልገሎቶችን ለማሳለጥ የሰው ሀይል፣ በጀት፣ ቁሳቁስ እና የውስጥ መመሪያ በፀደቁ የሀገሪቷ ህጎች መሰረት በማድረግ ይዘጋጃል፤

3/ የትስስር አካላት ከሚመለከተው ተቋም ወይም አካል ጋር በአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ዙሪያ በጋራ ይሰራል።

1/ An Intellectual Property and Technology Transfer Support Center shall be established in accordance with article 8 sub-article 1 and article 16 of Proclamation No. 1298/2023 to facilitate technology transfer activities carried out in each linkage actors;

2/ In accordance with sub-article 1 of article 5 of this directive, the linkage actors shall prepare manpower, budget, materials and internal guideline in accordance with approved laws of the country to manage the established center in each institution;

3/ The linkage actors shall work jointly with the relevant institution or entity in the area of intellectual property protection and technology transfer.

**አንቀጽ 6፡-የቴክኖሎጂ ሽግግር**

**Article 6፡ Technology Transfer**

1/ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራ የኢንዱስትሪውን ወይም የማህበረሰቡን ችግር ፈቺነት ባረጋገጠ መልኩ በትስስር አካላት የተለየ መሆን ይኖርበታል፤

1/ Technology transfer activities shall be identified by the linkage actors considering the problem of industry or society;

2/ በእያንዳንዱ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት ላይ ሁሉም የትስስር አካላት በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፤

2/ All parties shall work together in each technology transfer process;

3/ የተመረጠው የቴክኖሎጂ ሀሳብ ወይም የምርምር ውጤት ለተጠቃሚዎች መሸጋገር የሚችል መሆን ይኖርበታል፤

3/ The selected technology idea or research output shall be transferable to users;

4/ የሚዘጋጀው አነስተኛ የግልጋሎት ሞዴሉ በብዛት መመረት የሚችል እና ለኢንዱሰትሪው አገለግሎት የሚውል መሆን አለበት፤

4/ The small-scale utility model to be developed shall be mass-produced and suitable for industrial use;

5/ የትስስሩ አካላት ከማበልጸጊያ ማእከል ውስጥ የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች ገበያ ውስጥ ሲገቡ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማማከርና የመደገፍ ሥራ ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፤

5/ The linkage actors shall engage in consulting and supporting technologies emerging from the incubation center to be competitive when entering the market;

6/ የትስስር አካላት ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና አለማቀፋዊ ደረጃን በጠበቀ መልኩ በማዘጋጀት ተፈላጊነታቸውንና ተወዳዳሪነታቸውን እንዲጨምር የማድረግ ሥራ ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፤

6/ Linkage actors shall participate in utilization and development of local technologies in accordance with international standards to increase their desirability and competitiveness;

7/ የትስስሩ አካላት ከማበልጸጊያ ማእከላት የወጡ ቴክኖሎጂዎች ገበያ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ጀማሪ የንግድ ስራዎችን በመፍጠር የጋራ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችላቸው ስራ ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

7/ The linkage actors may engage in mutually beneficial activities by creating start-up businesses that can bring technologies from incubation centers to market.

## ክፍል ሦስት
## የትስስር አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

## Part Three
## Roles and Responsibilities of Linkage Actors

**አንቀጽ 7፡- የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ የወል ተግባር እና ኃላፊነት**

1/ ሁሉንም ዘርፎች የሚያገለግሉ በትስስር የሚተገበሩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ላይ በንቃት መሳተፍ፤

2/ በትስስር የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሳተፉ በዘርፉ ልምድ ያላቸው ተወካዮችን መመደብ፤

3/ የትስስር አካላት በየተቋማቸው በትስስር ለሚሠሩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን የሚያግዝ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና አእምሯዊ ንብረት ድጋፍ ማእከል ማቋቋም ይኖርባቸዋል፤

4/ በተቋሙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ማእከላት ወስጥ በቂ የሰው ኃይል እና መሰረተ-ልማት መሟላት፤

5/ በሀገራዊ፣ ክልል እና አካባቢያዊ የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ሂደት ውስጥ በመሳተፍ የጋራ ተጠቃሚነት እንዲመጣ አስተዋጽኦ ማበርከት፤

6/ የሀገራዊ የትስስር አደረጃጀቶች ውሳኔዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤

7/ ተቋማዊ የአእምሯዊ ንብረት ስርአት በመዘርጋት ለመምህራን፣ ለአሰልጣኞች፣ ለባለሙያዎች፣ ለተመራማሪዎች እና ለፈጠራ ባለሙያዎች የማበረታቻ መርሃ ግብርን ማዘጋጀት፤

8/ በትስስር የሚከናወኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች የአካል ጉዳተኞች፣ የሴቶች እና ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ችግር የሚፈቱ፣ ተጠቃሚ የሚያደርጉና ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ፤

9/ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ላይ ለሚሳተፉ የአካል ጉዳተኞች፣ የሴቶች እና ተጋላጭ የሆኑ

**Article 7: Higher education, technical and vocational training, research institutions, and industry shared role and responsibilities**

1/ Engaging in technology -related projects that serve all sectors with diligence and commitment;

2/ Select representatives with experience in the field to participate in the transfer of technology;

3/ Establishing a support center for technology innovation and intellectual property that assists technology transfer activities in their respective institutions;

4/ Ensure that sufficient human power and basic infrastructures are in the technology transfer support centers of the institution;

5/ Contribute to the mutually beneficial by participating in the process of technology transfer and development that can be used to solve specific national, regional and local problems;

6/ Implement accordingly decisions from the linkage organizational structures;

7/ Establish an institutional intellectual property system and develop an incentive program for teachers, trainers, professionals, researchers and innovators;

8/ Address, benefit and solve the problems of persons with disabilities, women and vulnerable communities through linkage technology transfer activities;

9/ Provide additional support and encouragement with special attention to persons with disabilities,

የማህበረሰብ ክፍሎችን ልዩ ትኩረት በመስጠት ተጨማሪ ድጋፍና ማበረታቻ ማድረግ፤

women and vulnerable communities involved in technology transfer activities;

10/ የትስስር አካላት በጋራ የምክር ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግር እቅድን መሰረት በማድረግ የራሳቸውን እቅድ ማዘጋጀት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት።

10/ Develop their own plans and prepare a performance report based on the linkage Council's Technology Transfer Plan.

**አንቀጽ 8፡- የትምህርት ሚኒስቴር ተግባር እና ኃላፊነት**

**Article 8፡ Roles and Responsibilities of the Ministry of Education**

1/ ሀገራዊ በትስስር የሚከናወኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማስተባበር፣ መምራት፤

1/ Coordinate and direct national technology transfer activities with relevant bodies;

2/ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ያሉ ትብብሮችን ማመቻቸት እና የትስስር አደረጃጀት መመስረት፤

2/ Facilitate cooperation around technology transfer and establish the linkage organization structure;

3/ በትስስር አካላት የተለዩት የቴክኖሎጂ ሽግግር ፍላጎቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በተመለከተ ውሳኔና አቅጣጫ በመስጠት፣ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ የትግበራውን ሂደት ይከታተላል፤

3/ Monitoring the implementation process by making decisions and direction regarding technology transfer needs and technologies identified by the linkage actors, designing implementation strategies;

4/ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ገዥ የህግ ማዕቀፎችንና ምክረ ሀሳቦችን ያዘጋጃል፣ ለትስስር ምክር ቤት ያቀርባል፣ በምክር ቤቱ ከፀደቁ በኋላ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

4/ In matters related to technology transfer, the ministry prepares legal frameworks and recommendations, provides them to the linkage council, ensures their implementation after approval by the council, and monitors their effectiveness;

5/በትስስር ምክር ቤት እውቅና አመታዊ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሽልማት እና ማበረታቻ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

5/ Establishes and implements annual technology transfer reward and incentive systems with the approval of the Linkage Council;

6/ በትስስር የሚገኘውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ሀብትን የትስስር አካላትን ፍትሀዊ ተጠቃሚ የሚያደርግ

6/ Ensure that there is a system that provides equitable access to the resources of technology

ስርአት መኖሩን ይከታተላል፤

transfer among the linkage actors;

7/ ለተሳካ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ማላመድ እና ሽግግር አገልግሎት ላይ የሚውሉ የተለያዩ መሰረተ-ልማቶችን በክላስተር ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ደረጃ እንዲመሰረቱ እና እንዲስፋፉ ያደርጋል።

7/ Establish and expand various infrastructures at the cluster or higher education institution level to be used for successful technology development, adaptation and transfer.

## አንቀጽ 9፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት

## Article 9፡ Roles and Responsibilities of Higher Education Institution

1/ በመማር-ማስተማር እና በምርምር ሥራ የቴክኖሎጂ መፍጠር፣ ማላመድ እና የማሸጋገር ስራን እስከ ጀማሪ የንግድ ድርጅት መፍጠርን እንዲሁም ቴክኖሎጂውን ገበያ ላይ ማዋልን ያካተተ ትግበራ አሰራር ስርአት ማዘጋጀት፤

1/ Develop an implementation system that includes the creation, adaptation and transfer of technology through learning-teaching and research and development activities to the creation of a start-up business enterprise and the commercialization of the technology;

2/ በትስስር ለቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ የሚውል ምቹ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን ማለትም ማበልጸጊያ ማእከላት፣ አሳላጮች እና ፓርኮች፣ ማቀነባበሪያ ክፍሎች እና ሀብት መመደብ፤

2/Allocate convenient infrastructure like incubators, accelerators and parks, processing rooms and resources for technology transfer work through linkage;

3/ የቴክኖሎጂ ፍላጎት እና አጋር አካላትን በመለየት የቴክኖሎጂ ሽግግር እምቅ አቅም ባለባቸው ቦታዎች ላይ ማተኮር፤

3/ Focus on areas with potential for technology transfer by identifying technology needs and partners;

4/ በሀገራዊ ደረጃ በተቋቋሙ የዘርፍ ኢንዱስትሪ ትስስር ፎረሞች የቴክኖሎጂ ሽግግር አላማዎች እና ኢላማዎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስርአት ማዘጋጀት፤

4/ Develop a system for implementing the technology transfer objectives and targets of nationally established sectoral industry linkage forums;

5/ በቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች ለተሳተፉ መምህራን፣ አሰልጣኞችና ተመራማሪዎችን ለማበረታታት የሚያግዝ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

5/ Establish a framework to encourage teachers, trainers, and researchers involved in technology transfer activities;

6/ በትስስር ውስጥ በተገኘ ቴክኖሎጂ አእምሯዊ ንብረት መብት በቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች

6/ Establish a system that enables teachers, researchers, and the institution to equitably share in

የተቋሙን መመሪያን ተከትለው ለተሳተፉ መምህራን፣ ተመራማሪዎች እንዲሁም ተቋሙን ከሚገኘው ጥቅም ተጋሪ የሚያደርግ ስርአት መዘርጋት።

the royalties from the intellectual property rights of technology acquired in linkages.

**አንቀጽ 10፡- የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት**

**Article 10: Roles and Responsibilities of Technical and Vocational Training Institute**

1/ ከትስስር አካላት ጋር በመመካከር የቴክኖሎጂ ሽግግር የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

1/ Develop a technology transfer system in consultation with the linkage actors;

2/ ለቴክኖሎጂ ልማት፣ ሽግግር እና ማላመድ የሚያገለግሉ እና ለከፍተኛ ትምህርት፣ ለምርምር ተቋማት እና ለኢንዱስትሪ ትስስር አገልግሎት የሚውሉ የራሳቸውን መሰረተ-ልማት እና ሀብት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤

2/ Provide access to their own infrastructure and resources that can be used for technology development, transfer and adaptation, to higher education, research institutes and industry for linkages activity purpose;

3/ ለኢንዱስትሪዎችና ኢንተርፕራይዞች እድገት የሚያመጡ ተስማሚ የቴክኖሎጂዎች ማበልጸጊያ እንዲሁም በትስስሩ በቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ለተሳተፉ ተመራማሪዎች፣ መምህራን እና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና ወይም የአቅም ግንባታ ማዕከል በመሆን ማገልገል፤

3/ Serve as a center to incubate appropriate technologies that promote development in industries and enterprises, and for skill training or capacity building for researchers, teachers, and professionals involved in technology transfer activities;

4/ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን መለየት፣ መምረጥ፣ መቅዳት፣ ማሻሻል፣ መፍጠር እና ማሸጋገር ላይ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

4/ To facilitate the identification, selection, adaptation, improvement, creation, and commercialization of suitable technologies based on the needs of the industry;

5/ ከከፍተኛ ትምህርት፣ ከምርምር ተቋማትና ከኢንዱስትሪ ጋር በመተባበር በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በአቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች ዙሪያ ያሉትን ክፍተቶች በመለየት ድጋፍና ክትትል ማድረግ።

5/ To collaborate with higher education institutions, research institutions, and industry to identify and monitor gaps in technology transfer and capacity building projects.

**አንቀጽ 11፡- የኢንዱስትሪ ተግባር እና ኃላፊነት**

**Article 11: Roles and Responsibilities of Industry**

1/ በተለያዩ የትስስር አደረጃጀቶች ማለትም በዘርፍ ኢንዱስትሪ ፎረም እና የትስስር አካላት አደረጃጀቶች ውስጥ ተሳትፏቸውን ማሳደግ፤

1/ Enhance their participation in various linkage organizational structure, including the Sectoral Industry Forum and other linkage actors activities;

2/ የኢንዱስትሪው ባህሪ መሰረት ያደረገ የቴክኖሎጂ ፍላጎት እና የሽግግር ስራዎች ለማሳለጥ የሚረዳ የአሠራር ስርአት መዘርጋት፤

2/ Establish framework to facilitate based on the nature of industry technology needs and transfer activities;

3/ በቴክኖሎጂ ሽግግር ውስጥ ለሚሳተፉ ተመራማሪዎች መደበኛ የስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት፤

3/ Develop formal training program for researchers involved in technology transfer;

4/ የኢንዱስትሪው ችግሮች በመለየት፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ ትልመ-ጥናት ማዘጋጀት፣ ለሚመለከታቸው የትስስር አካላት በዘርፍ ኢንዱስትሪ ፎረሞች አማካኝነት ለውሳኔ ማቅረብ።

4/ Identify, prioritize the problems of the industry, prepare a proposal, and submit it to relevant interdisciplinary bodies for decision through sectoral industry forums;

## አንቀጽ 12፡- የምርምር ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት

## Article 12: Roles and Responsibilities of Research Institute

1/ የምርምር ተቋማት ተግባራዊ ችግር ፈቺ ምርምር ላይ ትኩረት በመስጠት ከትስስር አካላት ጋር በጋራ መስራት፤

1/ Research institutions should focus on applied problem-solving research and work together with linkage actors;

2/ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ባገናዘበ መልኩ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ስራዎችን ማከናወን፤

2/ Carry out technology transfer and development activities in line with emerging technologies;

3/ ለከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና የኢንዱስትሪ ትስስር የአሰራር ስርዓት ውስጥ ምቹ የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግር ከባቢን መፍጠር።

3/ Create a favorable environment for technology transfer within the framework of higher education, technical and vocational training, and industrial linkage.

## አንቀጽ 13፡- የአዕምሮአዊ ንብረት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ማእከል ተግባር እና ኃላፊነት

## Article 13: Roles and Responsibility of Intellectual Property and Technology Transfer Support Center

1/የተቋሙን በአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ የሚያስፈልግ

1/ Prepare the necessary institutional Intellectual Property and Technology Transfer legal frameworks,

የተለያየ የህግ ማእቀፍ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል፣ ይከታተላል፤

implement after approval and follow up;

2/ ከተለያዩ አለም አቀፍ አእምሯዊ ንብረት ተቋማት የቴክኖሎጂ መረጃዎችን መፈለግና እና ማስቀመጥ የሚቻልበትን መንገድ እገዛ ማድረግ፤

2/ Provide assistance in searching and retrieving technology information from various international intellectual property organizations;

3/ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና አዕምሯዊ ንብረት አስተዳደር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

3/ Providing awareness training on technology transfer and intellectual property administration;

4/ የተለዩ የቴክኖሎጂ አስፈላጊ መረጃዎች እንደ አዲስነት፣ ከበፊቱ የሚለይበት ዘመናዊ ሁኔታ እና የህግ ጥሰት ማጥራት፤

4/ On-demand searches of information like novelty, state-of-the-art and infringement about the identified technologies;

5/ ስለ ኢንዱስትሪ የንብረት ህጎች፣ የቴክኖሎጂ ንግድ እና ግብይት መረጃ መለየትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

5/ Identifying and utilizing basic information about industrial property laws, technology business and marketing;

6/ በተቋም ደረጃ የማእከሉን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የመረጃ ቋት ማደራጀት፤

6/ Manage the database of users of Technology Transfer Support Center services at institutional level

7/ የተቋሙን አእምሮአዊ ንብረት ስራዎችን መምራት፣ ማስመዝገብ፣ የተገኘውን መብት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ አእምሮአዊ ንብረት መብቱን መከታተል፣ ኦዲት ማድረግ።

7/ Manage the intellectual property right activities of the institution, create conditions for the utilization of the acquired rights, monitor its intellectual property rights, conduct Intellectual property right audits.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

**አንቀጽ 14፡- የመተባበር ግዴታ**

የትስስር አካላት የትስስር ዓላማን ለማሳካት እና ይህን መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

**Article 14: Obligation to cooperate**

The linkage actors have an obligation to cooperate to achieve the purpose of the linkage and to implement this directive.

**አንቀጽ 15፡-. *መመሪያውን ስለማሻሻል***

*ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ትምህርት ሚኒስቴር ከትስስር ምክር ቤት ጋር በመተባበር ሊያሻሽል ይችላል።*

**Article 15: Amending the Directive**

This directive may be amended by the Ministry of Education in collaboration with the linkage Council, as necessary.

**አንቀጽ 16፡- *መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን***

*ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።*

**Article 16: Effective date of the directive**

This directive shall be effective as of the date registered by the Ministry of Justice and uploaded on the official website of the Ministry of Education.

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 21፣2017 ዓ/ም
ብርሃኑ ነጋ ቦንገር (ፕሮፌሰር)
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር
ሚኒስትር እና የትስስር ምክር ቤት ሰብሳቢ

**Addis Ababa, 29th May, 2025**
**Berhanu Nega Bonger (Professor)**
**Minister, FDRE, Ministry of Education and Chair of Linkage Council**